# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ቋፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 4 ግንቦት 28 2000 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

## ከሃዲ በሃገር ነግሶ፤ ሲጨርስ ሃገር ቆርሶ፤ ታሪክና ጀግንነት ረክሶ፣ ህዝብ በችጋር ኮስሶ፣ ዘረፋና አፈና ገደብ ጥሶ፣

## እስከመቼ ዝምታ? እስከመቼ ትእግስት?

## አንተ ስልጡን! አንተ ኩሩ ህዝብ! በቃኝ ውርደት! በቃኝ ባርነት በል! ምከር! ተሰባሰብ! ተባበር! ተነስ! ተነስ

## “መለስ መሬት የሰጠው ለሰሜን ሱዳን ነው። እኛም ድርሻችንን እንፈልጋለን!”

ይህ ቃል የተወሰደው በደቡብ ሱዳን ማላካል የተባለው ክፍለ ሀገር ሃገረ.ገዥ በትናንትናው እለት ወደ ኢትዮጵያ ከመለስ ዜናዊ ጋር ለመነጋገር ወደ አዲስ አበባ የሚያደርገውን የጉዞ መሰናዶ በሚያደርግበት ወቅት ነው። አገረ ገዥው እንዳለው፣ “በድንበር ጉዳይ የተደረገው ውል ሰሜን ሱዳንን እንጂ እኛን አይመለከትም። እኛም የሚገባን በኢትዮጵያ የተያዘብን መሬት አለ። የጉዞው አለማ ይህንንና በአካባቢው እየተባባሰ በመጣው የሴኩሪቲ ጉዳይ ላይ ከመለስ ዜናዊ ጋር ለመነጋገር ነው” ብሏል። የግንቦት ድምጽ በደረሰው ዘገባ መሰረት በሁሉም አቅጣጫና በሁሉም ነገር ተወጥሮ ያለው የመለስ አገዛዝ በደቡብ ሱዳን በኩልም ሃገር ቆርሶ በመስጠት በአካባቢው የሽምቅ ውጊያ በሚያደርጉ አማጽያን ላይ የደቡብ ሱዳን አስተዳደር እርምጃ እንዲወስድ መጠየቁ እንደማይቀር ይገመታል። በስልጣን ለመቆየት ተብሎ መለስ ዜናዊ ሃገር እየቆረሰና እየሸጠ በመጨረሻም የሚገዛው ሃገር የሌለው ሃገረ ገዥ ሆኖ ይቀራል የሚል አስተያየት በለበጣ መልኩ በኢትዮጵያውያን መሃል እየተነገረ እንደሆነ የግንቦት7 ድምጽ ከህዝብ ያሰባሰበው አስተያየት ይጠቁማል።የሃገረ ገዥውን የጉዞ ውጤት ወደፊት ለማቅረብ እንሞክራለን።

## አሳፋሪው የወያኔ ድርጊት በኮሌጅ ምሩቃን ላይ፣

የግንቦት7 ዜና ክፍል፣ ከመቀሌ ዩኒቨርሰቲ የደረሰው ዜና እንደሚያመለክተው፣ የዘንድሮ የዩኒቨርሰቲ ተመራቂዎች በሃገራቸው ስራ አግኝተው ለመኖር ከፈለጉ የወያኔ/ኢህአዴግ የአባልነት ቅጽ መሙላት እንዳለባቸው የተነገራቸው መሆኑን ነው። በእዚህ አግባብነት በሌለው አይን አውጣ ጥያቄ የተደናገጡ በርካታ ተማሪዎች ለቤተሰቦቻቸው ስልክ በመደወል የቀረበላቸውን አሳፋሪ ጥያቄ በመግለጽ የቤተሰቦቻቸውን ምክር ጠይቀዋል። ቤተሰቦቻቸውም በህዝብ የተተፋው ወያኔ/ኢህአዴግ ልጆቻቸውን ያለፍላጎታቸው ስራን ማስገደጃ በማድረግ አባላት ሆነው የጥላቻው ሸክም ተካፋዮች ለማድረግ የሚያደርገው ሴራ ቢያናድዳቸውም ለልጆቻቸው ምክር ለመስጠት ያልቻሉበት ሁኔታ እንዳለ የግንቦት7 ዜና ክፍል ለመረዳት ችሏል። *ወደ ገጽ 2 ዞሯል፤*

## ህዝብ በረሃብና በበሽታ ያልቃል፤ የሃገሩ ገዥዎች ግን ህዝብን ለመሰለል ከፍተኛ የሃገር ሃብት ያወድማሉ። ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## የቴዲ አፍሮ እስራት ፖለቲካዊ መሆኑን የእነፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ ጉብኝት አረጋገጠው።

እሁድ ግንቦት 24 2008 ዓ.ም በፕሮፌሰር ኤፍሬም የሚመራው የሽማግሌዎች ቡድን ቴዲ አፍሮን እስር ቤት በመሄድ ማነጋገሩን የግንቦት ድምጽ ዘጋቢ አሳውቋል። *ወደ ገጽ2 ዞሯል፤*

## «ሕጋዊ» ዘረፋ፤ የሽፍቶች ካፒታሊዝም በኢትዮጵያ። ብርሃኑ ነጋ (ካለፈው የቀጠለ)

ይህንን ንድፈሀሳባዊ ስሌት በጭንቅላታችን ይዘን ከእውነት ጋር የሚቀራረብ አንድ ምሳሌ በመስጠት እንዴት የንብረት ዝውውር እየተደረገ እንደሆነ በአጭሩ እንመልከት። አንድ ባለጊዜ የመንግስት ባለስልጣን ዘመድ ወይም ጉዋደኛ ወይም የሚስጥር የንግድ ሸሪክ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሰዎች ጋር ተመሳጥሮ አንድ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ ይገዛል። የሊዙ ዋጋ አንድ ሚሊዮን ብር ቢሆን የሚከፍለው 10 በመቶ ክፍያ አንድ መቶ ሺህ ብር ይሆናል። ቀሪውን ምንም ዋጋ በሌለው ወረቀት በሀያ አመት ውስጥ ይከፍለዋል። የመጀመሪያውን ክፍያ በቀላሉ ተበድሮም ቢሆን ይከፍላል። በዚህ መሬት ላይ በጣም ዘመናዊ የሆነ 80 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ህንፃ ለመስራት ይወስንና ለባንክ ማመልከቻ ያስገባል። ያስገባው የኢንቬስትመንት ጥናት እንደሚያሳየው (እውነት ነው ብለን እንውሰደውና) ህንፃው ሲከራይ በወር አንድ ሚሊዮን ብር ወይንም በአመት 30 ሚሊዮን ብር በሚከፈልበት ጊዜ የብር ዋጋ እንደሚያስገባ ያሳያል ስለዚህም ብድሩን መክፈል ይችላል። ይህ «ልማታዊ ባለሀብት» መበረታታት እንዳለበት ከአንድ የመንግስት ባለስልጣን ወይንም በሱ የተወከለ «ጉዳይ አስፈፃሚ» የሚነገራቸው የባንክ ባለስልጣኖች ለራሳቸው የሚቀበሉትን ተ ቀብለው ብድሩን ባለቤቱ ባስገመተው ከፍተኛ ግምት (ለምሳሌ 150 ሚሊዮን ብር) መሰረት ያፀድቃሉ። ባለቤቱም ብድሩ እንደተፈቀደለት ከተነገ ረው በሁዋላ ገንዘቡ ከመለቀቁ በፊት የህንፃው 30 ከመቶ ወጪ የሚሆን ማውጣቱን እንዲያሳይ ይነገረውና ስራ ይጀምራል። ይህንን ትንሽ አራጣም ተበድሮ ሊያደርገው ይችላል። ወይንም ብዙ ጊዜ እንደሚደረገው ትንሽ እንቅስቃሴ ካሳየ በሁዋላ ለባንኩ መሀንዲሶች ትንሽ ጉቦ ሰጥቶ የተጀመረው ሕንፃ 30 በመቶ ወጪ እንደወጣበት ይመሰክሩና የብድሩ ገንዘብ ይለቀቅለታል። ከተለቀቀለት ገንዘብ 80 ሚሊዮኑን ህንፃውን ለሚሰራው ለህንፃ ተቋዋራጭ ቢሰጠውና ከሚተርፈው 70 ሚሊዮን ውስጥ 50 ሚሊዮኑን ለመሬት ሊዝና ህንፃውን ለማስጀመር ለተበደራቸው አራጣ አበዳሪዎች ቢሰጥ በኪሱ ለመዝናኛ ወይንም ባለ መዋኛ የመኖሪያ ቤቱን ለመስራት በቂ ገንዘብ ይተርፈዋል ማለት ነው። የንብረት ዝውውር ታሪኩ ዝርፊያና መጠነ ሰፊ የንብረት ዝውውር እየተካሄደ መሆኑን የምናየው። *ወደ ገጽ 4 ዞሯል*

# ርእሰ አንቀጽ

## የመለስ አገዛዝ ከድጡ ወደማጡ መነከር የተለመደ ተግባሩ ሆኗል

ከግንቦት ምርጫ ሽንፈት በኋላ በህዝብ ላይ የደረሰውን ግድያ ለመሸፈን ሱማሌን ወረረ።የህዝቡን የብሄረተኝነት ሰሜት ለስልጣን ማራዘሚያ እጠቀምበታለሁ በሚል ስሜት።አሁን ደግም ህዝቡ የሚቀመስ አጥቶ በተቸገረበት ሰአት ለሱዳን መሬት ይሰጣል፣በምእራብ ታጣቂዎችን አስነስቶ ኦሮሞዎችን ያሳርዳል፣ምን አልባት ቀጥሎ ከኤርተራ ጋር ጦርነት ይቀሰቀስ ይሆናል።ይህን ሁሉ የሚያደርገው ያለ ምክንያት አይመስለንም።በምግብ ዘይት ውድነት፣በእህል ዋጋ ሰማይ ጠቀስነት፣በሸሮ እህል ዋጋ አልቀመስ ባይነት ህዝብ ኡኡታውን በሚያሰማበት ወቅት፣የዚህን ኡኡታ ጩህት ለማስቀየስና እንዳይሰማ ለመድፈቅ ነው ብንል ማጋነን አይመስለንም።በብልጥነቱ የሚመጻደቅ እንደመሆኑ፣በወረወርኩላቸው አጥንት ሲጯጯሁ፣ያኔ ግዜ አገኛለሁ፣በመሃሉ የውጭ አሳዳሪዎቼ ይደርሱልኛል ብሎ እንዳሰላ ግልጽ ነው።አይ.ኤም.ኤፍ የነብስ አድን ሃላፊነቱን በመውሰድ ”የቀረው የሁለት ወር ገንዘብ ብቻ ስለሆነ፣እባካችሁ የመለስ መንግስት እንዳይወድቅ እርጥባን ላኩ” እያለ የአለም መንግስታትን መማጠን ጀምሮአል።ይህ በእርጥባን ላይ የቆመ የለማኞች መንግስት፣ውሎ አድሮ ”በእንዴት እንግዛ” ጥያቄ ላይ በመሃሉ ልዩነት መፈጠሩ አይቀርም።ምልክቶቹም እየታዩ ነው።ባለፈው ሳምንት በመለስ ላይ የተሞከረው የግድያ ሙከራ የሚጠቁመን ነገር ቢኖር፣የህዝቡ ሰቆቃና እንግልት የቤተመንግስቱን በር እያንኳኳ መሆኑንና ”ከእንግዲህ በቃህ!” የሚለው ጥሪ ከህዝቡ አልፎ የመለስ አንጋቾች ጋር መድረሱን ነው።

ደግመን ደጋግመን ተናግረናል።የገዥዎቻችን ወታደሮችና አንጋቾች የኢትዮጵያ ልጆች መሆናቸውን።አጎት፣አክስት፣ወንድም እህት ያላቸው መሆኑን።በየእለቱ በቅርብ ርቀት የሚታዘቡት የገዢዎቻችን ቅምጥል ኑሮ የተሻሉ ምስክሮች እነሱው ናቸው።ጠዋት ማት ይታዘቡታልና።የነዚህን ሥልጣናቸውን የሚከላከሉላቸው ቅምጥሎችን ኑሮ ከስጋ ዘመዶቻቸው ቸነፈርና ረሃብ ጋር ለማወዳደርም ይችላሉ።ልዩነቱንም ለመቀበል ከማይችሉበት አፋፍ እየደረሱ ነው።”የወገኖቻችን ስቃይ ያክትም!” የሚሉበት ቀን በጣም ደርሷል። ለጊዜው ዘብ በመለዋወጥ ገዢዎቻችን እፎይታ የሚያገኙ ይመስላቸው ይሆናል።ይህ ግን በጣም ጊዜያዊ መፍትሄ ነው እንላለን።እውነተኛው መፍትሄ የሃገሪቱን የፖለቲካ ችግሮች ሁሉ ሊፈታ የሚችለውን፣ህዝብ በመረጣቸው እንደራሴዎች ሊተዳደርበት የሚችልበትን መፍትሄ መቀበልና ለተግባራዊነቱም መትጋት ነው።ከዚያ መለስ የሚደረገው ሽርጉድ ሁሉ ከንቱ ነው እንላለን።የራስን ህዝብ አቅም ማሰባሰብና፣በነጻነትም ሃገሪቱን ለመወንጨፍ የሚችልበትን ዕድል ዘግቶ የፈረንጅ ኮረጆ አንጋጦ በመጠበቅ የሚገኝ ነገር የለም።ወይን በአሜሪካን የሚገኙ ጥቂት የአፍሪካ እበላ ባይ ነጋዴዎችን ሰብስቦ ”ታላቁ የአፍሪካ ታላቁ የፖለቲካ መሪ” አድረጉኝ ብሎ ጉቦ በመስጠትና ይህንንም እንደ ዜና በማቅረብ ራስን ማወደስ ሃገራችን ኢትዮጵያ ለምትገኝበት ማጥና ቀውስ የማይመጥን ባዶ ቀልድ ነው እንላለን።መወደድ በራስ ህዝብ እንጂ በሰው ሃገር ስደተኛ ቢሆን ምን እርባና አለው?

### አሳፋሪው የወያኔ ድርጊት በኮሌጅ ምሩቃን ላይ፣...

ግንቦት ዜና ሪፖርተር እንደሚለው ከሆነ፣ በግንበት 97 ብሄራዊ ምርጫ ወያኔ/ኢህአዴግ በህዝብ ተተፍቶ ከተሸነፈና በአይነ ደረቅነትና በጉልበት ሰልጣን ላይ ለመቆየት ከወሰነ በኂላ፤ ሌላ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እየተከተለ የሚገኘው ስልት ገበሬውን በመሬቱ፣ የመንግስት ሰራተኛውን የኮሌጅ ምሩቁን በስራው፣ ነጋዴውን በበድር አለማግኘትና በታከስ ማብዛት እያስፈራራ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ግለሰቦችን የድርጅቱ ቅጽ እንዲሞሉ በማድረግ ህብረተሰቡን የወያኔ አባል በሆኑና ባልሆኑ ግለሰቦች በመካከፈል አርስ በርሱ እንዲናከስ ማድርግ ነው፡፡ የዩኒቨርስቲ ምሩቃንንም ካለፈው አመት ጀምሮ ከመመረቃቸው በፊት በስራ በማስፈራራት የአባልነት ፎርም ሲየስሞላ ዘንድሮ የመጀመሪያው እንዳልሀነ ተገልጽዋል፡፡ ባለፈው አመት በተመሳሳይ መንገድ ምሩቃን ፎርም እንዲሞሉ ተደርገው፣ የተወሰኑት ተመራቂዎች በተለያዩ የመንግሰት መስሪያ ቤቶች ልክ በደርግ ግዜ ይደረግ እንደነበረው፣ ስራ ኖረም አልኖረም መደልደላቸው ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ግን በየአመቱ ከዩኒቨርስቲዎች የሚመረቀው ተማሪ ቁጥሩ በጣም ብዙ በመሆኑ የተነሳ፤ ተማሪዎች አሺ ብለው የአባልነት ቅጽ ቢሞሉም በጣት ለሚቆጠሩ የስርአቱ አቀንቃኞች ካልሆነ በስተቀር የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ድቀትና የመንግስት በጀት እጥረት የተቀረውን በብዙ ሽህ የሚቆጥር ምሩቅ ስራ ሰጥቶ ደሞዝ መክፈል የማይችል መሆኑን ተማሪዎቹ እራሳቸው የሚያውቁት ጉዳይ እንደሆነ ግንቦት ዜና ለመረዳት ችሏል፡፡ ወያኔ/ኢህአዴግ 4 ሚሊዮን አባል አለኝ፣ አራት ሚለዮን ተወዳዳሪ አቅርቢያለሁ በማለት የመመጻደቅበት

### አሳፋሪው የወያኔ ድርጊት በኮሌጅ ምሩቃን ላይ፣...

የተጋነነ የአባለት አሃዝ የተገኘው እንደ ተማሪዎቹ በግድ ቅጽ እያስሞላ የመዘገበውን በሙሉ ቆጥሮ መሆኑን የግንቦት7 ዜና ሪፖርተር ገልጽዋል፡፡ በእዚህ መንገድ በኑሮውና በስራው ተገዶ አባል የሆነ ሁሉ ያለፍላጎቱ ያዋረደውን ኢህአዴግ አምሮ የሚጠላ፤ ውርደቱን ለመበቀል ያደባ የተቃዋሚዎች ደጋፊ እንጂ፣ የወያኔ አገልጋይ ከቶውኑም እንደማይሆን ታዛቢዎች መግለጻቸውን ሪፖርተራችን በዘገባው አክሎበታል፡፡

ይህ አይነት የአባላትን ቁጥር በግድ በማብዛት የህዝብ ተቀባይነት መለኪያ ለማድረግ መሞከር ቀድም ሲል ለደርግ ኢሠፓም እንዳልሰራ ወያኔ ውስጥ ያሉ ኢሠፖዎች የሚያውቁት ጉዳይ ነው ሲሉ አንድ አንድ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

ህዝቡም በጣም በርካታ ግለሰቦች ተገደውና ማስፈራሪያ ደርሷቸው የአባልነት ቅጽ የሞሉ መሆናቸውን በመረዳት፣ ይህም ህብረተሰቡን እርስ በርሱ ለመከፋፈል ታስቦ የተጠነሰሰ ሴራ መሆኑን በማወቅ፣ በእዚህ መንገድ ተገደው አባል ከሆኑት ጓደኞቹና ዘመዶቹ ጋር የማይጣላና የማይቃቃር መሆኑን በተግባር እየገለጸ ነው በማለት ሪፖርተራችን ዘግቧል፡፡

በእዚህ መንገድ ተገደው የወያኔ/ኢህአዴግ አባላት ለሆኑት ግለሰቦች ህዝብ የሚያስተላልፈው መልእክት፤ ‹ወያኔን ከውስጡ ሆናችሁ ምሰጢሩን አውጡበት፣ ሌብነቱን ክህደቱን የአድሎና የዘረኛነት ስራውን በማሰረጃ ደግፉችሁ አጋልጡት፣ ህዘብን ለመሰለል፣ በህዝብ ላይ አደጋ ለመጣል ሲያሴር አስቀድማችሁ ለህዝብና ለህዝብ ወጎኖች መረጃ አስተላልፉ፣ ድሮም ቢሆን ሃገር ሲወረር የውስጥ አርበኛ ከጠላት ካምፕ ገብቶ ይሰራ ነበርና እናንተም ይህን ስራ በመስራት ሃገራዊ ግዴታችሁን ተወጡ፤ ለእዚህ ድርጊታቸሁ የአርበኛነት ሽልማት እንጂ የህዝብ ጥላቻ አታተርፉም፡፡ አትፍሩ አትስጉ እኛ አንጠላችሁም፡፡ ውሎ አድሮ የሚጠላቸሁ ወያኔ እራሱ እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ በህዘብ ላይ ከፍተኛ መከራና ስቃይ የሚያዘንቡትን የወያኔ/ ኢህአዴግ እውነተኛ ሰላዮችና ገዳዮች ከእናንተ መለየት አያቅተንም፣ የሚል መሆኑን የግንቦት7 ዜና ለመረዳት ችሏል፡፡

### የቴዲ አፍሮ እስራት.....

በጉብኝቱ ወቅት ሽማግሌዎቹ ከቴዲ አፍሮ ጋር ያደረጉት ወይይት ዝረዝሩ ባይታወቅም፣ ታዋቂውን ገጣሚ፣ ሙዚቃ አቀነባባሪና ድምጻዊ አርቲስት እስር ቤት ድረስ ሂደው ሽማግሌዎቹ ማነጋገራቸው የቴዲ ጉዳይ የወያኔ መንግስት እንደሚለው የተራ ወንጀል ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ጉዳይ እንደሆነ ያረጋግጣል በማለት ብዙዎችን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እያነጋገረ እንደሆነ ዘጋቢያችን አሳውቋል፡፡ ወደ ገጽ 3

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ የቀድሞ
የአዲስ ዜና እና የነጻነትጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፡ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣አቶ መሰፍን አማን፤አቶ ቸኮል ጌታሁን፤ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ።

ከገጽ 1 የዞረ

## ህዝብ በረሃብና በበሽታ ያልቃል፤

ህዝብ የሚገለገልባቸውን የኢንተርኔት እና የሞባይል አገልግሎቶች ለመቆጣጠር እና በወያኔ የስለላ መረብ ወስጥ ለማስገባት፣ ወያኔ የዘመኑን የኤሌክትሮኒክ የስለላ መሳሪያዎችንና ኤክስፐርቶችን በመግዛት ከፍተኛ ወጪ ማድርጉን፣ የተለያዩ የሚድያ አውታሮች ቀደም ብለው መዘገባቸውን በማስታወስ፤ ይህ የወያኔ የስለላ ፕሮጀክት፣ የስለላውን መሳሪያ መጠቀም የሚችሉ በርካታ ወጣቶችን በማሰልጠን በሙሉ ሃይሉ የሚንቀሳቀስበት ምእራፍ ላይ መድረሱን የግንቦት7 ዜና ዘጋቢ አስታውቋል።

የግንቦት7 የዜና ምንጭ አያይዞ እንደገለጸውም በአዲስ አበባ፣ አይቤክስ ከሚባለው የቴሌ የማሰልጣኛ ጣቢያ፣ ከተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ወደ 3 ሽህ የሚጠጉ ወጣቶች የተለየ ስልጠና የተሰጣቸውና አሁንም እየተሰጣቸው ነው። በእዚህ ማእከል ውስጥ ስልጠናውን ከሚሰጡት የውጭ ዜጎች በተጨማሪ፣ በኤሌክትሮኒክ የግንኙነት ዘዴዎች ላይ ከፍተኛ እውቀት ያላቸው፣ ለአገዛዙ በከፍተኛ ብር በመገዛት በእዚህ እኩይ ተግባር ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያንም እንዳሉ የግንቦት7 የዜና አቅራቢ መረዳት ችሏል። የእነዚህ ዜጎች ማንነት በጥንቃቄ ከተጣራ በኋላ ስማቸው ለግንቦት7 እንደሚተላለፍ የተናገሩ ሃገር ወዳድ ተባባሪዎች ማግኘቱንና ይህ መረጃ እንደደረሰው ለተበዳዩ ህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ሪፖርተራችን አስታውቋል።

በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያላችው እነዚሁ ወጣቶች የቴሌኮምኒኬሽን ባለሙያተኛ በሚል ስም የስለላ ሥራውን የጀመሩ ሲሆን፣ ሌሎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ደግሞ ስልጠናውን ጨርሰው ስራ ባይጀምሩም ከቴሌ መስሪያ ቤት ደሞዝ እየተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል። ከአንዳንዶቹ ወጣቶች በተገኘው መረጃ መሰረት፣ ያለምንም ስራ፣ ደሞዝ እየተከፈላቸው እንዲቆዩ የተደረጉት፣ ለእዚህ ስለላ ስራ ታማኝ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ለማጣራት ወያኔ/ኢህአዴግ የጀመረውን የስለላ ስራ እስኪጨርስ ድርስ እንደሆነ ይናገራሉ።

በሌላ በኩል የወያኔ/ኢህአዴግ ጠቅላይ ሚንስቴር፣ ከፍተኛ ባለስልጣናትና የጸጥታ ሹሞች ብቻ የሚጠቀሙበት ቪስታ (VISTA) የሚባል ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት መሆኑን የግንቦት 7 ሪፖርተር ገልጾ፣ ይህም አገልግሎት በቀጥታ ሱልልታ ከሚገኘው የሳተላይት ጣቢያ ጋር የተገናኘ መሆኑን አስረድቷል። እንደ ግንቦት 7 የዜና ምንጭ፣ ባለሥልጣኖቹ የሞባይልም ሆነ የኢንተርኔት አገልግሎቶችን የሚያገኙት VPN ( virtual private network) በሚባል የግል ኔትወርክ አማካይነት ሲሆን፣ የሞባይልም ሆነ የኢንተርኔት አገልግሎቶች ለህዝብ በተዘጉበት ጊዚያት ገዥዎቹና የፀጥታ ሹሞቹ እንደፈለጉ የሞባይልም ሆነ የኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። በሃገሪቱ ውስጥ በኢንተርኔት አገልገሎት መስጠት ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ለንግድ ስራቸው የሚያስፈልጋቸው የግል፣ የትምህርትና የስልጠና ተቋማትና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የኢንተርኔት ግልጋሎት፣ የወያኔ/ኢህአዴግ ገዥዎች እንዳሻቸው እንደ ቧንቧ ውሃ መዝጋትና መክፈት የቻሉበት ሁኔታ የመጣው ለራሳቸው ብቻ የሚጠቀሙበት የኢንተርኔትና የሞባይል አገልግሎት ስላላቸው መሆኑ ታውቋል። ገዥዎቹ ስልጣናቸውን ለመንከባከብ ሲሉ በየግዜው በሚዘጉት የኢንተርኔትና የሞባይል አገልግሎት የተነሳ፣ በሃገር ኢኮኖሚና በህዝብ ላይ የሚደርሰው መንገላታት ደንታ የማይሰጣቸው መሆኑን በየግዜው ግልጋሎቱን እንዲዘጉ ትእዛዝ ከሚሰጣቸው ባለሙያተኞች የግንቦት7 ዜና አቅራቢ መረዳት ችሏል።

ከዚህም በተጫማሪ መለስም ሆነ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖቹ የሚጠቁሙባቸው የሞባይል ስልክ አይነቶች (G8 ) የተባሉ ሲሆኑ፣ እነዚህ አይነቶቹ ስልኮች የተለያዩ የኔትወርክ አገልግሎቶችን በቀላሉ መጠቀም የሚያስችሉ ናቸው ተብሏል።

በአሁኑ ግዜ የሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ባዶ በሆነበት፣ አመታዊ የአገዛዙ በጀት ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ እጥረት ባሳየበት ወቅት፣ ህዝብ በረሃብ መርገፍ በጀመረበት፣ የኑሮ ውድነት ሃገሬውን ባሳበደበት አስከፊ የመከራ ዘመን፣ አሁንም የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ለስለላ መሳሪያና ለስለላ ስራ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪና በጀት መድቦ በተጠናከረ መንገድ መንቀሳቀስ መቀጠሉን ለስለላው ስራ ቅርበት ያላችው ሃገር ወዳዶች ለግንቦት 7 ዜና አስታውቀዋል።

ከእዚህም ጋር በማያያዝ ወያኔ የደረሰበትን የባጀትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለማሟላት የአለም ባንክን፣ የአለም አቀፉን የገንዘብ ድርጅትና የምእራብን መንግስታት ብድርና ምጽዋት እንዲሰጡት የልመና ፌስታሉን ይዞ በሚዞርበት ወቅት፣ ይህ አገዛዝ ምን ያህል ሃብት ህዝብን ለመሰለልና ለማፈን እያባከነ እንደሆነ፣ የወጣቶቹን የቴሌ ስልጠና እና ሌሎቹንም የአፈና መዋቅሮቹን ወጪዎች በመጥቀስ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሊያጋልጡት፣ አገዛዙ የሚጠይቀውን የገንዘብ እርዳታ የሰብአዊ መብት ጥሰትንና የዴሞክራሲ መብቶች ረገጣ ሳያቆም እንዳይሰጠው የተለመደውን እንቅስቃሴያቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው የሚል ጥሪ ሪፖርተራችን ካነጋገራቸው ዜጎች ማግኘቱን አስታውቋል።

በሃገራችን ተከታታይ ገዥዎች ህዝብን በስለላና በጉልበት አፍነው ለመግዛት ያደረጉት ሙከራ ያልተሳካ፤ ሁሉም ተዋርደው ከስልጣን እንደተባረሩ ሁሉ ወያኔ/ኢህአዴግም በህዘብ እንዲህ በተተፋበት ሁኔታ የፈለገውን የስለላና የአፈና አቅም ቢያጠናክር መጨረሻው ከቀድሞዎቹ አገዛዞች የተለየ እንደማይሆን፣ የወያኔን የስለላ ድርጊት ዝርዝር የሰሙ የእድሜ ባለጸጋ አረጋዊ ለግንቦት7 ዜና ገልጸዋል። ይህ የአረጋዊው ትንበያ በቅርቡ እውን ይሆናል የሚል እምነት የአብዛኛው የሃገሪቱ ዜጋ እምነት እየሆነ መምጣቱን ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙ በማተት ዘጋቢያችን ዜናውን አጠናቋል።

ከገጽ2 የዞረ

## የቴዲ አፍሮ እስራት.....

በማከታተልም ሽማግሌዎቹ ለቴዲ አፍሮ ከወያኔ ኢህአዴግ ይዘውት የመጡት መልእክት ይኑር አይኑር ባይታወቅም፣ መልእክቱ ወያኔ ከእዚህ በፊት እንደ ለመደው በሽምግልና ስም፣ ያለጥፋታቸው ያሰራቸውን ግለሰቦች፣ ያላጠፉትን አጠፋሁ ብለው ይቅርታ እንዲጠይቁና ወያኔ የሰራውን ወንጀል በተበዳዮቹ ላይ ለጥፎ ፕሮፓጋንዳ ለማካሄጃ ሲጠቀምብት ከኖረው ስለቱ ውጭ ሊሆን አይችልም የሚል ግምት እንዳለ ሪፖርተራችን አብራርቷል፡፡ ወያኔ/ኢህአዴግ ቴዲን አፍኖ የሚያሰቃየው፣ የመለስን ጸረ-ኢትዮጵያ መርሃ ግብር ቴዲ በድምጹ እያሰናከለበት ስላስቸገረው እንደሆነና ቴዲን በማሰቃየትና በሽማግሌዎች ሴራ ጥሎ በመዋረድ፣ ከሚወደው ህዝብ ጋር ለማቆራረጥ ታቅዶ እንደሆነ የሚገምቱ እየተበራከቱ መምጣታቸውን የደረሰን ሪፖርት ጨምሮ ገልጿል፡፡

## <u>የሽፍቶች ካፒታሊዝም ከገጽ 1የዞረ</u>

በባንክ አሰራር መሰረት ይህ ሰው ቢያንስ ለሁለት አመት ህንጻው እስከሚያልቅና እስከሚከራይ ብድሩን ከመክፈል እረፍት ያገኛል:: የሁለቱ አመት ወለድ በዋናው ብድር ላይ ተደምሮ (ወደ 24 ሚሊዮን ብር) ከሁለት አመት በሁዋላ የብድሩ አጠቃላይ መጠን በቀላል ስሌት ወደ 174 ሚሊዮን ብር ያድጋል:: ብድሩ በአስር አመት ማለቅ ያለበት ቢሆን የመጀመሪያ ክፍያውን በሚከፍልበት በሶስተኛው አመት ላይ ከተከራዮቹ የሰበሰበውን በወር አንድ ሚሊዮን ብር ይከፍላል:: የዚህ ሰውዬ የመጀመሪያው የ150 ሚሊዮን ብር ብድር በአመቱ አሁን ባለው አነስተኛ ው ወደ 30 በመቶ በሚጠጋው የዋጋ ግሽበት ምክንያት ወደ 105 ሚሊዮን ብር ዝቅ ብሎአል:: በሁለተኛው አመት ክፍያውን ሲጀምር ወለዱን ጨምሮ ያለበት 174 ሚሊዮን ብር ከ60 ከመቶ በላይ ቀንሶ ወደ 70 ሚሊዮን ብር ብቻ ይሆናል ማለት ነው:: ይህ ሰውዬ እውነተኛ ብር ተበደሮ በያመቱ ዋጋውን ያጣ ወረቀት ነው ማለት ነው የሚከፍለው:: በአንፃሩ በየአመቱ ከሚያገኘው (ከባንክ ክፍያ ከሚተርፈው) ገቢ በተጨማሪ የብድር ጊዜው ከአስር አመት በሁዋላ ሲያልቅ ምንም ዋጋውን የማያጣ ምናልባትም እየጨመረ የሚሄድ በመቶ ሚሊዮኖች የሚገመት ንብረት ባለቤት ይሆናል ማለት ነው:: ይህን ንብረት ከየት አመጣው? መቼም ሰርቶ አይደለም:: ካፒታሉን አውጥቶ አይደለም:: እቆጥባለሁ ብሎ ገንዘቡን ባንክ ካስገባ ደሞዝተኛ፤ ከባንክ መበደር የማይችል የሸጠውን ባንክ ከሚያስቀምጥ አነስተኛ ነጋዴ፤ ከጡረተኛ...ወዘተ:: እነኝህ ሁሉ ሰዎች ላባቸውን አንጠፍጥፈው የሰሩበትን ገንዘብ ዋጋውን እያጣ ነው በስውር እየተዘረፉ ያሉት:: ይህ ግልፅ ዘረፋ በትክክለኛ መንገድ በሚሰራ የከበርቴ ስርአት ሊፈፀም አይችልም:: ማንኛውም የኢኮኖሚ ባለሙያ እንደሚያውቀው እውነተኛው የባንክ ወለድ የባንኮች የማበደሪያ ወለድ ከዋጋ ግሽበት መጠን ጋር ተቀንሶ የሚገኘው ወለድ ነው:: አሁን ኢትዮጵያ ባለው የማበደሪያ መጠንና የዋጋ ግሽበት መጠን መሰረት እውነተኛው የማበደሪያ ወለድ ከዜሮ በታች ከ22 በመቶ በታች ነው:: ይህም ማለት አንድ ከባንክ ብድር ለማግኘት የቻለ ሰው ከባንክ ለሚበደረው ለእያንዳንዱ ብር እሱ ወለድ እየከፈለ ሳይሆን ባንኩ 22 ከመቶ ወለድ ይከፍለዋል ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እውነተኛውን የካፒታሊስት ህግ የሚከተል ቢሆን በአሁኑ ጊዜ የሚኖረው የባንክ የማበደሪያ ወለድ ቢያንስ 30 ከመቶ መሆን ነበረበት ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ግን እነኝህ ህንፃ የሚሰሩት ባለሀብቶች ሊሰሩ ያዳግታቸዋል:: እድገት የሚመስለው ነገርም ለማስመሰል እንኳዋን እንዳይቻል ባለበት ይቆማል:: አሁን ባለው ሁኔታ ግን በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ይመታል:: አቶ መለስ እድገት አመጣሁ ብለው መፎከርና ስለዚህም ስለ መብት፤ ስለዴሞክራሲ አታውሩ የሚለውን ደፋርና አይን ቀርጥፎ የበላ የፍፁም ንቀት ቱልቱላ ለመንፋት ያስችላቸዋል፤ አብረውም አጋሮቻቸውን ከባዶ ተነስተው የጠገቡ ዲታዎች ያደርጉዋቸዋል::

በዚህ አይነት ድምሩ ዜሮ የሆነ የንብረት ዝውውር ሁሉም ሰው ሊጠቀም አይችልም:: ሁሉም ሰው ልበደር ብሎ ባንክ ቢሄድ ለዚያ ሁሉ የሚሆን ገንዘብ የለም:: ስለዚህም የግድ ጥቂት ባለጊዜዎች ብቻ ናቸው ሊጠቀሙ የሚችሉት:: ለዚህም ነው ብድር ለተወሰኑትና ጥሩ ንክኪ ላላቸው ብቻ የሚታደለው:: የዚህ አይነት ጥቂት አዳዲስ ሚሊየነሮች ከብዙሀኑ ህዝብ ኪስ እየወሰዱ ነው እየበለፀጉ ያሉት:: የእነኝህን አይነት ዘራፊዎች ህንፃዎች እያሳዩ ነው እድገት መጣ የሚሉን:: በእርግጥ ከመንግስት ጋር ሳይመሳጠሩ የሚሰሩ የሉም ማለት አይደለም:: ነገር ግን የመንግስት ባለስልጣኖችና ቡችላዎቻቸውን ለመጥቀም የተ ፈጠረው ይህ ስርአት እነሱንም (ከባንክ መበደር እስከቻሉ ድረስ) በሰፊው እየጠቀማቸው መሆኑን መርሳት የለብንም:: ለዚህም ሊሆን ይችላል እነኝህም ሰ ዎች መንግስትን ፊት ለፊት ለመኮነን ትንሽ የሚቸገሩት:: መንግስት ከህዝቡ እየተበደረ የሚሰራው መንገድም ልክ እንደዚሁ ከአስቀማጩ ህዝብ የተዘረፈ ነው:: በ30 ከመቶ የዋጋ ግሽበት መንግስት ከህዝቡ ለሚበደረው እያንዳንዱ ብር የሚከፍለው 70 ሳንቲም ብቻ ነው ማለት ነው:: ለዚህም ነው መንግስት በጣም እየተበደረ የዋጋ ግሽበቱን ከቁጥጥር ውጪ እንዲወጣ ያደረገው:: እነሱ ኬክ እስከበሉ ድረስ ሌላው የሚበላው ቢያጣ ደንታ የማይሰጣቸው ጭራቅ አዲስ ከበርቴዎች ነው እየተፈጠሩ ያሉት:: የዚህ የዋጋ ግሽበት በሽታ ብዙ እንድምታ ነው ያለው:: ከላይ ያቀረብኩት አነስተኛ ምሳሌ ግን ከንብረት ዝውውር ጋር በተ ያያዘ ላሳይ የፈለግሁትን ነጥብ ያሳየ ይመስለኛል::

በዚህ መልክ ከድሀውና ከመሀከለኛ ገቢ ካለው ደሞዝተኛ (የመንግስት ሰራተኞች፤ ወታደሮች፤አስተማሪዎች፤ገበሬዎች፤ ሌሎች ሰራተኞችና ጡረተኞች) እየተመዘበ ረ ጥቂት ሰዎችን ሀብታም የሚያደርግ ሂደት፤ እየፈጠረ ያለው ሰፊ ልዩነት ምን የፖለቲካ እንድምታ አለው? አዲሶቹ የገዢ መደቦች ይህን እንዴት እያሰሉት ነው?

የዚህ ፖለቲካዊ እንድምታ እንዲገባን እነመለስ ቀደም ብለው ሲነግሩን ወደነበ ረው ማርክሳዊ ትንተና ይመልሰናል:: ፖለቲካ የአንድ አገር ኢኮኖሚ ነፀብራቅ ነው፤ ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረ ነው ለዘላቂው ፖለቲካውን የሚቆጣጠረው:: አሁን ባለው የአለም ሁኔታ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ስርአት የከበርቴ ስርአት ከመሆን በቀር ምርጫ ስለሌለው ፖለቲካውን የሚቆጣጠረው የከበርቴው ክፍል ነው የሚሆነው:: ስለዚህ እኛና የእኛ ደጋፊዎችን በሙሉ በአጭር ጊዜ ከበርቴ ስናደርግ ብቻ ነው በፖለቲካው የበላይነታችንን ይዘን መቀጠል የምንችለው:: ይህን ሀብት በአስቸኳዋይ ለማካበት ያለን ብቸኛ አማራጭ ደግሞ የፖለቲካ ስልጣኑን እንደዚህ እንደአሁኑ ሙሉ በሙሉ በምንቆጣጠርበት ሰአት እንዲህ አይነቱን ከፍተኛ የንብረት ዝውውር ማድረግ ስንችል ነው ከሚል በጣም አደገኛ ና መሰሪ ትንተና የመጣ፤ ታስቦበት የሚሰራ ስራ ይመስላል:: በርግጥ አስበውበት ሆነም አልሆነም ግን ውጤቱ አንድ ነው:: በአስቸኳዋይ ልናስቆመው ካልቻልን (ልናስቆመው የምንችለው ደግሞ በጉልበት የያዙትን የፖለቲካ ስልጣን መንጭቀን ማውጣት ስንችል ብቻ ነው) አገራችን ከምንጊዜውም በላይ ጥቂት በስራቸው ሳይሆን በስልጣናቸውና ከባለስልጣኖች ጋር በመሞዳሞድ ከፍተኛ ንብ ረት ያካበቱ የሽፍታ ከበርቴዎችና ከነሱ ፍርፋሪ የሚለቅሙ ህሊናቸውን የሸጡ ሆዳሞች እየተንደላቀቁ ፤ ይህን ምቾታቸውን ለመከላከል ደግሞ ህዝቡን እየ ረገጡና እየገደሉ፤ የሚኖሩባት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሆዳቸውን እያከኩ፤ የሚላስ የሚቀመስ አጥተው ከመቃብር በላይ ከኑሮ በታች የሆነ የምሬት ኑሮ ብዙሀኑ የሚኖርባት፤ ብዙሀኑም ለችግሩ እግዚአብሄርን እያማረረ የሚኖርባት አገር እንድትሆን ነው እያዘጋጁዋት ያለው::

ይህ የነሱ ምኞት ግን ሙሉ ለሙሉ ይሳካል ማለት አይደለም:: በዚህ ሁኔታ የተማረረው ብዙሀን ምሬቱ አፎቱን ሞልቶ ሲፈስና ሞትን የማይፈራበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ይህንን የእነሱን የእድገት ምልክት የሆኑ ፎቆች ድምጥማጣቸውን ሊያጠፋ፤ ትንሽ ብር ያለውን ሁሉ እንደ ደመኛ ጠላቱ የሚያይበት ብሎም ካላጠፋሁ የሚልበት ፍፁም ያልተረጋጋና የአገሪቱን አብሮ መኖር የሚፈታተን ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበት እድል የዚያኑ ያክል መሆኑን ከዚህ ድሀ በዘረፉት ሀብት የሚበሉት ጥሬ ስጋና የሚጠጡት ውስኪ ጭንቅላታቸውን ፍፁም ካልጋ ረዳቸው፤ እነሱም ሳይገነዘቡት አይቀሩም:: ለዚህም ይሆናል ብልጥ ነን ብለው የሚያምኑትና ይህ ነገር እንደማይዘልቅ የተረዱት ከዘረፉት ሀብት ገሚሱን በጊዜ ወደ ውጪ አገር የሚያሸሹት::

በአንፃሩ ለአገሪቱ በጎ የሚያስቡ ሀይሎች እንዲህ አይነት አደገኛ ሁኔታ እስከሚፈጠር ዝም ብለው የሚያዩበት ህሊና ሊኖራቸው አይገባም:: ይህ የተ ከመረ ችግር በቀላሉ ሊመለስ የማይችልበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ትግላቸውን አስተባብረው፤ የእነኝህን ሀፍረተ ቢስ ሌቦች የስልጣን እድሜ ማሳጠር አለባቸው:: በዚህ ነውረኛ መንግስት ምትክ የሚቁዋቁዋመው መንግስት በእውነትም ዴሞክራሲያዊ፤ በህዝብ ፈቃድና ይሁንታ ብቻ የሚያስተዳድር፤ ተ ጠሪነቱም ለመረጠው ህዝብ ብቻ የሆነ መንግስት እንደሆነ ህዝቡ ካወቀና ይህንንም ለማምጣት የሚደረገው ትግል የሚከተለውን የትግል አቅጣጫ ለህዝቡ በደንብ ካመላከተ፤ ያልተደራጀና በግብታዊነት የሚመጣ የህዝብ ቁጣ ከሚያመጣው ለውጥና ትርምስ ይልቅ ህዝቡ ይህን ትግል ተቀላቅሎ የአገራችንን አደገኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ ወደ ተረጋጋ ማረፊያ ይወስደዋል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ::

**ኩሩ ህዝብ ነን!**
**አገራችንን እናድን !**
**መብታችንን እናስከብር!**
**እንተባበር! እንነሳ! እንታገል!**
**እንደ ቀደምቶቻችን ታሪክ እንስራ!**